የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእአኮ)
SOLIDARITY COMMITTEE FOR ETHIOPIAN POLITICAL PRISONERS (SOCEPP)

መጋቢት 19/2005

# ወያኔና ሳውዲ አረቢያ የሚፈጽሙትን ግፍ እናውግዝ!

አረመኔው የወያኔ አገዛዝ ወደ ሳውዲ አረቢያ ለዘመናዊ ባርነት ከ 45 ሺ ያላነሱ ወጣት ኢትዮጵያውያን ሴቶችን ሊልክ ከመስምማቱ ሌላ ዛሬ ደግሞ ወደ የተባበሩት አረብ ኤሚሬትስም ያልተናነሰ ቁጥር ሊያግዝ መነሳቱን በዕብሪት አሳውቋል። በሳውዲ አረቢያ ኢትዮጵያውያን በአረመኔ ዘረኝነት እየተጠቁና አሰቃቂ ስየል እየተቀበሉም መሆናቸው በመረጃ የተረጋጠ ነው።

ወጣት ሴቶችን ለዘመናዊ ባርነት በመሸጥ ወያኔ በሚሊዮን የሚቆጠር ዶላር ወደ ኪሱ እያስገባ ነው። ከወደ ትግራይ ለዚህ ዘመናዊ ባርነት የሚሰደዱት ቁጥር ወደ ዜሮ መሆኑም መታየት ያለበት ነው። ሳውዲ አረቢያ፤ ሌባኖን፡ የመን፤ ካታር ወዘተ ማለትም የአረብ ሀገሮች በአጠቃላይ ዘረኞችና ለኢትዮጵያውያን ገሃነም መሆናቸው ደግሞ የተረጋጋጠ ነው። ሌሎች ብዙ ለዜጎቻቸው የሚቆረቆሩ ሀገሮች (ፊሊፒንስ፤ ኢንዶኔዚያ፤ ማሌዚያ ወዘተ) ወደ አረብ ሀገሮች ዜጎችን ልከን ለስቃይና ሞት አንዳርግም ሲሉ ወያኔ ግን ገንዘብ ካገኘሁ በሚል አማራጭ ያጡ ዜጎችን በሺዎች ለስቃይና ለሞት እየዳረገ ነው። በአረብ ሀገሮች በሳምንት ከአስር በላይ ኢትዮጵያውያን ለሞት መዳረጋቸው የተዘገበ ጉዳይ ነው። ይህንን በዝምታ ማሳለፍ ከስህተት በላይ ወንጀልም ሐጢያትም/ሀራምም ሊባል የሚችል ነው። በሳውዲ እስር ቤቶች ከሁለት መቶ ሀምሳ በላይ ኢትዮጵያዊ እስረኞች አሉ። ክርስቲያን ተብለው፤ ቀጣሪዎች አሳስረዋቸው ወዘተ… የሳውዲ ፖሊሶችና ባልስልጣኖች ዜጎቻችንን አቢድ--ባርያ የሚሉና የሚያሰቃዩ ዘረኞችና ዕብሪተኞች ናቸው። ሴት ዜጋችንን በአደባባይ ሰቅለዋል። ስንቱ ተወርቶ! በሳውዲና በአረብ ሀገሮች ላይ ተቃውሞ ለማሰማት ስንነሳ ግን በቅድሚያ እህቶቻችንን ልጆቻችንን በሚሸጠው ወራዳና ከሃዲ የወያኔ አገዛዝ ላይ ውግዘት ማሰማት የሚጠበቅብን ነው።

ሳውዲ አረቢያ በኢትዮጵያውያን ላይ ዘረኛ ግፍ እየፈጸመች ነው። በሌሎች አረብ ሀገሮችም በመታጀብ ላይ ናት። መውጪያ መግቢያው የጠፋችውና የተቸገሩ ወጣት ኢትዮጵያውያን የዚህ ግፍ ሰለባ ሆነዋል። በሺዎች ደረጃ! ይህንን እስከመቼ በዝምታ እናየዋለን? በሁሉም ቦታ በሳውዲና ሌሎች የአረብ ሀገሮች ኤምባሲዎች ( ሌባኖን፤ ካታር፤ ሊቢያ፤ ኩዌት ወዘተ..) ደጃፍ ተቃውሞና ቁጣን ማሰማት ይጠብቅብናል። ወያኔንም ማጋለጥና ማውገዝም እንዲሁ።


INJUSTICE ANYWHERE IS INJUSTICE EVERYWHERE
SOCEPP, POSTFACH 51213, BERLIN 13372,GERMANY
SOCEPP, 30 RIGA COVE, WINNIPEG,MB R2P 2Z7,CANADA
E MAIL: SOCEPP @AOL.COM
WEB SITE: WWW.SOCEPP.DE